מעלים
הקרן למען בעלי מקצועות שוחקים (ע"ר)

ስውራተኞችህ ብቁ ባለሙያ ስራተኞች እንዲሆኑ፣ በሃገሪቱ ልዩ የገንዘብ እርዳታ ሥልጠና ሲቀበሉና፤ ድርጅትህ በጎበዝና በታታሪ ሰራተኞች ሲበለጽግ ፤ ይህ ህብረተሰባዊ ኢኮኖሚ ነው ፤

እኛ ማን ነን ?

" ማዓጋሊም " በመንግስታዊ እርዳታ የተቋቋመ ሲሆን ዋናው ዓላማውም ከ - ፩· ዓመት በላይ ለሆኑ ሰራተኞችና ከ - ∨ ዓመት በላይ በጉልበት ስራና ዓቅምን በሚያቆረቅቁ ስራዎች ለሚሰሩ ሰራተኞች ድጋፍ ነው ፤ ወይም የ - ፫· ዓመት የስራ ልምድ ላላቸው የዕድሜ ገደብ የለባቸውም ።

ድካም የሚሰማቸው ሰራተኞች ፤ ልዩ የስልጠና ጊዜ ፤ የስራ እድገት ወይም ስራ የመቀየር አስፈላጊነት፣ ይህ ሁሉ በሃገሪቱ የገንዘብ ዓርዳታ ይከናወናል ። አሰሪውን በስራተኞቹ ባለሙያነት ፤ ደስተኛ በሆኑ ሰራተኞችና ከፍ ያለ የምርት ውጤት በሚሰጡ ሰራተኞች ይኖሩታል በዚህም ይደሰታል ።

ዘርፎች

ኬሬን " ማዓጋሊም " ሁለት ዓይነት ዋና ዋና ዘርፎችን ትሰጣለች ፤ ከ አሰሪው ጋር ሙሉ በሙሉ ግንኙነት ማስረግ ሲሆን፣ ይህም የሚሆነው በአሰሪውና በስራተኛው ጥሩ ተሳትፎ በማደረግ የድርጅቱን ዕድገት ለማምጣት ሲባል ነው ።

የሰራተኞች ዕድገትና ብልጽግና ዘርፍ ፤

በዚህ ዘርፍ ድርጅቱ ሙሉ በሙሉ ወጭውን ይሸፍናል ፤ የሰራተኞችን ዕድገት ወይም የስራ ልምድ መቀየር ፤ በዚህ የትምህርት ጊዜ ተስማሚና የድርጅቱን የምልመላ/ምርጫ ስርአቶች ያሟሉ ሰራተኞች ከድርጅቱ የመኖሪያ የሚሆን የገንዘብ ድጎማ ይቀበላሉ ።

ቀደም ብሎ ጣረታ ስለመውጣት ዘርፍ ፤

አስከሁለት ዓመት ቀደም ብለው በኋላ ጥሮታ ለሚወጡ ሰራተኞች ፤የመኖሪያ ክፍያ ይሰጣል፣ ይህም በህጉ መሰረት ቀደም ብሎ ጥሮታ መውጣታቸውን ያመቻቻል ፤ ይህ ዘርፍ ዋና ዓላማው በገንዘብ ምክንያት ቀደም ብለው ጥሮታ ለመውጣት ለሚፈልጉ ሰራተኞች ሲሆን፣ ይህም ና በስራው ጤናና በሥራ ውጤቱ ላይ ጉዳት እንዳያስከትል ታስቦ ነው ።

የሚያደክሙ ስራዎች እነማን ናቸው ?

አንድ ስራ የሚያደክም ስራ ነው የሚባለው ሁለት ነገሮችን ሲያካትት ነው ፤

- ለብዙ ጊዜ ክባድ ዕቃዎችን መሸከም ፤
- ብዙ ጊዜ መቆምን የሚጠይቅ ስራ ፤
- በዓደገኛ የአየር ጸባይ የሚሰሩ ስራዎች ፤
- ብዙ ጫጫታ ያለበትና የጀሮ መስማትን የምያወርድ /የሚያደነቁር ሥራና ቦታ ፤
- ብዙ ሙቀትና ወይም ቅዝቃዜ ያለበት ስራ ቦታ ፤የማቀዝቀዢ መሳሪያ ውጤት ሳይሆን ፤
- ከአየር ጸባዩ ጋር ግንኙነት የሌለው በቀዝቃዛ ቦታዎች መስራት ፤
- በአደገኛ ንጥረ ነገር አካባቢ መስራት ፤
- አደገኛ ሽታ ባለበት አካባቢ መስራት ፤
- ለብዙ መንገደች በክባድ መኪና በማሽከርከር የሚጓዙ ፤
- ከአደገኛ ከፍታ ቦታዎች የሚሰሩ ፤
- በጊዜ ክፍፍል የሚሰሩ ስራዎች ቢያንስ ፥ የቅይይር ስራዎች ማታ/ለሊት የሚሰሩ ፤
- የህክምና ችግሮች በሃኪሞችና በቢቱዋህ ልኦሚ ድርጅት ስብሰባዎች የሚፈራረቁበት ፤

ከአሁኑ ጀምረህ ስራተኞችህ ከዚህ ድርጅቱ ዕርዳታ ይገባቸዋል ወይስ አይገባቸውም የሚለውን መርምርና የዓመት በጀት መቀበል ትችላለህ ፤

የዚህን ድርጅት የተለዩ ስጠታዎች ለመጠቀም በዚሁ ዓመት ከእኛ ጋር በስልክ ግንኙነት ይፍጠሩ ፤ የስልክ ቁጥር

1-800-071-144

ወይም በድረ ገጽ www.magalim.org.il

ההסתדרות ביחד בשבילך
נשיאות הארגונים העסקיים
משרד הכלכלה
משרד האוצר